ዘመነ ጽጌ /የአበባ ወራት/

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ሁልጊዜም አንድ ዓመት በአራት ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላል።

እነዚህም፦

1. መፀው /የአበባና የመከር ጊዜ/
2. ሐጋይ ወይም በጋ /የፀሐይ ጊዜ/
3. ፀደይ /የበልግ ጊዜ/
4. ክረምት /የዝናም ጊዜ/ እየተባሉ ይጠራሉ።

አሁን ያለንበትም ዘመን ዘመነ ጽጌ ወይም ወርኀ ጽጌ/የአበባ ወራት/ በመባል ይታወቃል። በዚሁ ወርኀ ተራሮች አበቦችን በዛፎች ጫፍ ላይ ተክለው እንደ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ ስናይ የሚሰማን ደስታ ከመጠን ያለፈ ነው።

አበቦች በጥበበኞች እጅ የተሠሩ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጠሩ በመሆናቸው ከግዕዛን ፍጥረታት መካከል አበቦች እጅግ ለዓይንም ሆነ ለልቡና አስደሳች ነገር አይገኝም። አበቦች ቡብዙ ወገን ይጠቅሙናል። ምንም እንኳ እንደ ፍሬ ዕለቱን ቁርጠን ባንመገባቸው ለዓይን ደስታ ከአበቦች የበለጠ ባለመገኘቱ በደስታም በሃዘንም እንፈልጋቸዋለን። ብዙ ደራስያን ስለ አበቦች ተናግረዋል ዘምረዋል ጽፈዋል። ከደራስያኑ ተቀድመው ጠቢቡ ሰሎሞን ስለአበቦች ሲናገር «እነሆ ክረምት አለፈ ዝናሙም አልፎ ሔደ አበቦችም በምድር ላይ ተገለጡ የዜማም ጊዜ ደረሰ» ብሏል። ይህን በጆሮ መስማት ብቻ ሳይሆን በዓይናችን አይተን ለመረዳት ብንፈልግ ከከተማ ወጣ ብለን ትንሽ ከተጓዝን በኋላ ዓይናችንን አቅንተን እንመልከት እነሆ አበቦች በየተራራውና በየሸንተረሩ በየጫካውና በየመስኩ ፈክተዋል። ንቦች አበባቸውን ቀስመው ማርን ለማበርከት ያማረ ዜማቸውን እያሰሙ ማልደው ተነሥተው ወደየሥራቸው ይሠማራሉ። ወፎች በልዩ ልዩ ጽምፅ ይዘምራሉ። እንስሳት የለመለመ ሣርን ነጭተው የጠራ ውኃ ተጎንጭተው ይዘላሉ።

ልምላሜዎችና አበቦች ከነፋስ ጋር በአንድነት ሆነው የሹክሹክታ ድምጻቸውን ያሰማሉ። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን የእግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት አስተውለን ስንመለከት የሚሰማን አድናቆት ከፍ ያለ ነው። በዚህ ወራት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለ አበቦች የተሰማውን ደስታ በልዩ ልዩ መዝሙር ገልጿል። ክርስቶስም አበቦችን የተስፋና የእምነት ምሳሌ አድርጎ ተናግሯል። ዕፀዋት ዝናምን ከእግዚአብሔር ተቀብለው አበቦችን ለዓይን መዓዛቸውን ለአፍንጫ ይገብራሉ። ዕፀዋት ይህን ሲሠሩ እኛ ዝም ብለን መመልከት የለብንም። የሚገባውን ገጸ በረከት ይዘን ወደ እግዚአብሐር መቅረብ ይኖርብናል። እኛ ከግዕዛን ፍጥረታት ተለይተን የከበርንና የላቅን ስንሆን በሥራ ከእነርሱ በታች ሆኖ መገኘት የለብንም። አበቦች ለሰው ዓይን እንደሚያስደስቱ እኛም መልካም ሥራ በመሥራት እግዚአብሔርን ማስደሰት አለብን።

ምግባራችንና እምነታችንን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አበባ የፈካ ሆኖ እንዲገኝ ሁልጊዜ ለበጎ ሥራ መታጠቅ ያስፈልጋል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት አይለየን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር